ዕሌኒም በዚህ ምልክት መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ አውቃ ቁፋሮ አስጀመረች ። በእግዚአብሔር ቸርነት መጋቢት ፲ ቀን ከተቀበረበት ወጥቷል ። የጌታ መስቀል በወጣም ጊዜ ብዙ ተአምራትን አድርጓል ንግሥት ዕሌኒም መስቀሉን በክብር አሲዛ በጐልጐታ ቤተ መቅደስ አሠርታ በዚያ አስቀመጠችው ። ለዚህ ታላቅ ዕድል የተመረጠችው ቅድስት ዕሌኒም መስቀሉን ባወጣች በዓመቱ በ፫፻፳፰ ዓ/ም አርፋለች ። ሥራሽ ያውጣሽ ተብላ በባሏ ወደ ባህር የተጣለችው ቅ/ዕሌኒ ንጽሕናዋና ታማኝነቷ ይህን ለመሰለ ክብር አበቃት ።

በዚህ መሠረት ቅ/ዕሌኒ መስቀሉን ለማውጣት ደመራ ያስደመረችበት ዕለት መስከረም ፲፮ ቀን በየዓመቱ በታላቅ ድምቀት በመላዋ ቤ/ክርስቲያናችን ዘንድ ይከበራል ።

በግላዊ ኑሮአችንም ሆነ በማኅበራዊ ኑሮአችን ንጹሐንና ታማኞች ሆነን ከተገኘን ፈጣሪያችን ለታላቅ ክብር እንደ ሚያበቃን ጥርጥር የለውም ። እግዚአብሔርም ንጹሐን ሰዎች አይጥላቸውም ለጊዜው የረሳቸው ቢመስልም የኋላ ኋላ በክብር ይገልጻቸዋል ። ተንኮለኞችን ግን በተንኰላቸው ይይዛል ። በቆፈሩት ጉድጓድ እነሱ ይወድቃሉ ። ስለዚህ የዕሌኒን በፈጣሪዋ ላይ ያላት የጸና እምነት ለባሏ ያላት ታማኝነት ለሁላችንም አርአያ የሚሆን ነው ። የቅድስት ዕሌኒ ጸሎቷ በረከቷ አይለየን ።